# እኛ ካለፈ ታሪካችን ጋር ታርቀናል!

## ክፍል ሁለት

**አሜን ተፈሪ** 09-05-17

በመጣጥፌ ክፍል አንድ ለርዕሰ ጉዳዬ መነሻ የሆነኝን የሰባት ወራት የአሜሪካን የፖለቲካ ውሽንፍር አውስቼ ወደሐገራችን በመመለስ ካለፈው ታሪካችን ጋር ስለመታረቅ ጉዳይ በመሰረትነት የሚቆመውን ህገ መንግስት በማንሳት መቆሜ ይታወሳል። ቀጣይ ፤ሀሳቤን እነሆ።

አዎን የኢትዮጵያ ብሔር፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከትናንቱ ታሪክ ለመታረቅ ሲሞከሩ ትናንት ምን እንደሚመስል ገልጸው ነው። ሆኖም ሐሳባቸው <<ያለፈው ግንኙነት የተዛባ>> መሆኑን በመጥቀስ የተገደበ አይደለም። መጪው ጊዜ ምን እንዲመስል እንደሚፈልጉም ይጠቅሳሉ። በመጪው ጊዜ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መፍጠር እንደሚፈልጉ አስረግጠው ይጠቅሳሉ። ታዲያ መጪው ጊዜ ያማረ እንዲሆን፤

- የህግ የበላይነት የተከበረበት፤
- የብሔር፣ ብሔረሰብ መሠረታዊ መብቶች የተከበሩበት፤
- የጾታ እኩልነት የተረጋገጠበት፤
- ባህሎች እና ሐይማኖቶች ካላንዳች ልዩነት እንዲራመዱ ማደረግ የሚያስችል ስርዓት መገንባት አስፈላጊ መሆኑን በግልጽ አስፍረዋል።

እንዲህ ያለ ሰርዓት መፍጠር በሐገራችን ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም እና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ማድረግ እንደሚያስችልም ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ህዝቦች <<ይህን ማድረግ አስፈላጊ ነው>> ብለው ያለፉት ጉዳይ አይደለም። ይልቅስ አጽንዖት ሰጥተው፤ <<ይህን የማድረጉ አስፈላጊነት ጽኑ እምነታችን ነው>> ሲሉ አስረግጠው ተናግረዋል። ይህ ጽኑ እምነታቸው እውን እንዲሆን ከታሪክ የወረሷቸው የተዛቡ ግንኙነቶች መኖራቸውን አንስተው በኩርፊያ አልተቀመጡም። እነዚህን የተዛቡ ግንኙነቶች ለማረም እንደሚቻልም ያላቸውን እምነት በመጥቀስ፤ ስለመጪው የጋራ ዕድላቸው ይናገራሉ። <<በተለያዩ መስኮች እና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረው>> አብረው የኖሩ በመሆናቸው ያፈሩት የጋራ ጥቅም እና አመለካከት መኖሩን ጠቅሰው፤ <<ይህን የጋራ ጥቅማችንን፣ መብታችንን እና ነጻነታችንን በጋራ እና በተደጋጋፊነት>> እናሳድጋለን ይላሉ። ይህንን ዓላማ እና ፍላጎታቸውን ለማሳካት አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት ጉዳይ እጅግ አስፈላጊ መሆኑንም አጽንዖት ሰጥተው ይናገራሉ።

ታዲያ ለዚህ እምነታቸው፣ ዓላማቸው እና እምነታቸው ማሰሪያ ይሆን ዘንድ አንድ የቃል ኪዳን ሰነድ አኑረዋል። ይህም የቃል ኪዳን ሰነድ ህገ መንግስቱ ነው። መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት በተመሠረተው የህገ መንግስት ጉባዔ የተረቀቀውን ህገ መንግስት ህዳር 1987 ዓ.ም አጽድቀዋል። አንድ ሐገር ካለፈ ታሪኩ ጋር ሊታረቅ የሚችልው በዚህ ዓይነት መንገድ ነው።

ሐገር ካለፈ ታሪክ ጋር መታረቅ የሚችለው ያለፈውን በማውሳት ብቻ አይደለም። መጪው ዘመን ምን እንደሚመስልም በግልጽ በመመልከትም ነው። የኢትዮጵያ ህዝቦች ይህን አድርገዋል። ሁለቱም ጉዳዮች (ያለፈው እና የመጪው ዘመን ሁኔታ) በኢፌዴሪ ህገ መንግስት መግቢያ ላይ ጥንቅቅ ብለው ሰፍረዋል።

ታዲያ ገዢው ፓርቲ ይህን ህገ መንግስት በማረቀቅ እና በማጽደቅ ሂደት ጉልህ ድርሻ ነበረው። በማርቀቅ እና በማጽደቅ ብቻ አይደለም። ይህን ህገ መንግስት ተግባራዊ በማድረግ ረገድም ወሳኝ ድርሻ የነበረው እርሱ ነው። የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ዓላማችን፣ እምነታችን እና ፍላጎታችን ብለው የጠቀሷቸውን ጉዳዮች ለማሳካት ወይም ህገ መንግስቱን ህይወት ያለው ለማድረግ የሚደነቅ ትግል እና ጥረት አድርጓል። ያለፈው የተዛባ ታሪካችን እንዲታረም የመጀመሪያ እርምጃ የወሰደው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ መሆኑም የሚታወቅ ነው።

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ያለፈ ታሪካቸውን አይተው፤ ከታሪካቸው የተመለከቱትን የተዛባ ግንኙነት በማረም፤ የተናጠል ጥቅማቸውን በተናጠል ለማሳካት መራመድን አልመረጡም። የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ልዩ ትኩረት ያደረጉት፤ በህገ መንግስቱ መግቢያ በተለያየ አገላለጽ ደጋግመው ያሰፈሩት፤ የጋራ ጥቅምን በጋራ እና በመደጋገፍ ለማሳከት ጥረት የማድረግን አስፈላጊነት ነው። ይህ ሐሳባቸው በህገ መንግስቱ መግቢያ ቃል በቃል ተጠቅሶ እናገኘዋለን። <<ጥቅማችንን፣ መብታችንን እና ነጻነታችንን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ...>> ሲሉ ፍላጎታቸውን በግልጽ አስፍረዋል። ህገ መንግስቱ የጠባቦች እና የትምክህተኞች ሰነድ አይደለም።

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በማንኛውም ኃይል ግፊት አሁን ከያዙት ጎዳና መውጣት አይፈልጉም። <<በትግላችን እና በከፈልነው መስዋዕትነት የተገኘው ሰላም ዘላቂ እንዲሆን እና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲሰፍን>> እንፈልጋለን ይላሉ። ወደ ኋላ የተመለከቱት ወደፊት ለመጓዝ ነው። በርግጥ፣ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በትግላቸው እና በመሰዋዕትነታቸው ያገኙት ሰላም እና ዴሞክራሲ ዘላቂነት ያሳስባቸዋል። ዘላቂ ሰላም እና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ መገንባት ይፈልጋሉ። ይህ ሊሆን የሚችለውም የህግ የበላይነትን ሲረጋገጥ፣ የግለሰብ እና የብሔር/ብሔረሰብ መሠረታዊ መብቶች ሲከበሩ፣ በጾታ፣ በባህል እና በሐይማኖት እኩልነት መረጋገጥ ላይ የተመሠረተ ስርዓት ሲገነቡ እንደሆነ ተናግረዋል። ይህን በማድረግ ደግሞ አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር እንደሚፈልጉም ግልጽ አድርገዋል።

ታዲያ ዘላቂ ሰላም እና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ ለማጽናት በሚያደርጉት ትግል እንቅፋት ሆነው ሊደቀኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ነቅሰው በማውጣት እነዚያን ችግሮች ከመንገዳቸው ማስወገድ ይኖርባቸዋል። ነገን ያማረ ለማድረግ ዛሬ መሥራት ይኖርባቸዋል። የወደፊቱን ሁኔታ በትክክል መተንበይ የሚቻለው፤ ከትናንት ታሪክ ጋር በደንብ ታርቆ፤ <<ነገን>> ዛሬ በመሥራት ነው። ነገን በትክክል ለመተንበይ የሚቻለውም <<ዛሬን>> በአግባቡ በመሥራት ነው። ከህብረተሰብ ህይወት አንጻር <<ነገን>> መሥራት የሚቻለው፤ በወጣቶች እና በህጻናት ላይ አትኩሮ በመሥራት ነው። ከትናንት ታሪካችን ጋር ዛሬ ታርቀን ወደፊት መቀጠላችንን ማረጋገጥ የምንችለው የተተኪውን ትውልድ ወይም የወጣቶችን አስተሳሰብ በተገቢው ሁኔታ ዛሬ በመቅረጽ ነው።

በእኔ አስተያየት ኢትዮጵያ ካለፈ ታሪኳ ጋር ለመታረቅ የሚያስችል ጥሩ ዕድል አግኝታለች። ኢትዮጵያ ካለፈ ታሪኳ ጋር መታረቋን መካድ አይቻልም። በዚሁ ልክ፤ በአስተሳሰብ ድሁርነት ወይም በግል የፖለቲካ ጥቅም ስሌት በትናንት ሰንሰለት የታሰሩ ቡድኖች እና ግለሰቦች መኖራቸው የሚታበል አይደለም። ታዲያ ሐገሪቱን ካለፈ ታሪኳ ጋር የመታረቅ ዕድል እንድታገኝ ትግል ያደረጉ ኃይሎች፤ የወደፊቷ ኢትዮጵያ ተረካቢ የሆኑ ወጣቶችን፤ በትናንት አሉታዊ ታሪክ (በሁለት መንገድ) ታስረው የወደቁት ወገኖች ሰለባ እንዳይሆኑ መስራት ይጠበቅባቸዋል። የወደፊት ተስፋዎቻችን ከትናንት ጋር ታስረው የወደቁ ቡድኖች ምርኮ እንዳይሆኑ ነቅተን መጠበቅ ይኖርብናል።

የጉዟችን እንቅፋት የሆኑ እና እጅግ ተጻራሪ የሆኑ አቋሞችን የሚያራምዱ ሁለት ቡድኖች አሉ። ተጻራሪ አመለካከት ያላቸው እነዚህ ወገኖች፤ በአመለካከት የተለያዩ ሆነው ሳለ አንድ የሚደርጋቸው ጉዳይ አለ። ሁለቱም በትናንት የታሰሩ ናቸው። ይህ አንድ ያደርጋቸዋል። አንዱ ያለፈው ታሪክ እንከን አልባ መሆኑን በማስረዳት፤ ሌላው ያለፈው ታሪክ የሰቆቃ ብቻ መሆኑን በማሳየት የተጠመዱ ናቸው። እናም ሁለቱም በትናንት አሮጌ ሰንሰለት የታሰሩ ናቸው። አንዱ ያለፈውን በማሽሞንሞን - ሌላው ያለፈውን በማከፋፋት፤ አንዱ ትናንትን በመናፈቅ - ሌላው ትናንትን በማናናቅ የወደፊቱን ማየት የተሳናቸው ሆነዋል። አንዱ ያለፈውን ናፋቂ - ሌላው ባለፈው ነገር ጨቃታ አካኪ ነው።

ሁለቱም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ካለፈው ታሪካቸው ጋር ታርቀው ወደፊት ለመራመድ የሚሹ መሆናቸውን ለማየት አልቻሉም። የተለያየ የፖለቲካ ካባ እንደደረቡ በትናንት ችካል ታስረው ወድቀዋል። ሁለቱም ሐገሪቱ ካለፈ ታሪኳ ጋር በመታረቅ የአዲስ ስርዓት ግንባታ ፕሮጀክት መጀመሯን ተረድተው፤ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መጪው <<ጥቅማችንን፣ መብታችንን እና ነጻነታችንን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ ቆርጠን በመነሳት...>> በሚል አዲስ ሐገር ለመገንባት የሚያደርጉትን ጥረት መደገፍ የማይችሉ ናቸው።

በሌላ በኩል፤ ሐገሪቱን ካለፈ ታሪኳ ጋር አስታርቆ የሐገር ግንባታ ፕሮጀክት ይዞ የሚታገለው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይል፤ አንዳንዴ በሁለቱ የትናንት ኃይሎች ጩኸት እየተደናገረ ወይም በዛሬ ሁኔታ ተውጦ እየተዘናጋ፤ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ህልም የሚጨናገፍበትን አደጋ ሊጋብዝ ይችላል። እንደ ጓያ ነቃይ የፊት የፊቱን ነገር ብቻ እየተመለከተ፤ የወደፊቱን ሁኔታ በእጃቸው ይዘው የቆሙትን ወጣቶች እና ህጻናት በመዘንጋት ለውኽንብር የሚጋለጡበትን ክፍተት ፈጥሯል። የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፤ ከዛሬ ኮረብታ ወዲያ ማዶ ያለውን፤ ከአድማሱ ባሻገር አርቀው የሚመለከቱትን ዓለም የሚናፍቁ ናቸው። አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሐገሪቱን ከትናንት ታሪኳ ጋር ማስታረቅ ብቻ ሳይሆን፤ ህዝቡን ከነገ ተስፋው እንዲገናኝ ሊያደርጉት ይገባል። ይህ ሥራ በተቋማት ግንባታ ሊገለጥ ይችላል። ተቋም ማለት ህንጻ ወይም መሥሪያ ቤት አይደለም። ተቋም ማለት የታወቀ እና በግልጽ የተቀመጠ የአሰራር ስርዓት ነው። በሌላ አገላለጽ፤ የህግ የበላይነት ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። ይህ እውን እንዲሆን የህግ የበላይነትን ያለማወላወል በማክበር እና በማስከበር ረገድ መትጋት ያስፈልጋል። ለተተኪው ትውልድ ይህን የአሰራር ባህል አውርሶ፤ ተተኪው ኃይል ከዚህ ሳይፈናቀል መኝዝ ይኖርበታል። ይህን ለማድረግም በወጣቶች እና በህጻናት ላይ ትኩረት አድርገን መሥራት ይገባናል።

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት እፈልጋለሁ። የኢትዮጵያ ወጣቶች እና ህጻናት አንድ የጋራ ብሔራዊ መዝሙር (በተለያየ ቋንቋም ቢሆን) እንዲዘምሩ ሳናደርግ፤ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የቃል ኪዳን ሰነዳቸው (በህገ መንግስቱ) ያሰፈሩትን አንድ የፖለቲካ እና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር እንዴት ይቻለናል? እናም፤ እንዲህ ያሉ ጉዳዮች መታየት አለባቸው።